# ኢትዮጵያችን

***የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን***

**ኢትዮጵያችን ልዩ ዕትም ቅጽ** 1 **ቁጥር** 2 **የካቲት ፳፫ ቀን ፪ ሺህ ፱ ዓ.ም.**


# <u>ትናገር አድዋ</u>

https://www.youtube.com/watch?v=gWFHRGeJ2kM

አድዋ የኢትዮጵያ፣ አድዋ የአፍሪካ፣ አድዋ የጥቁር ህዝብ ታሪክ ነው። በዕለተ ጊዮርጊስ የካቲት ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ስምንት ሀገር ወራሪ ጦር በምሥራቅ አፍሪካ አከርካሪው የተመታበት ዕለት። የዓለም ድሀ ሀገሮችን የናቀና ጦር መሣሪያውን የተማመነ ኃይል በጋሻ ጎራዴ የተንበረከከበት፣ የነፃነት ጮራ ከወደ ምሥራቅ አፍሪካ የፈነጠቀበት፣ ታሪካዊ የድል ቀን አድዋ። ትናገር አድዋ። ትመስክር አድዋ።

አድዋ :- ጀግኖች የሞቱልሽ፣ ድል ያበሰሩብሽ፣
የተዘመረልሽ፣ የተዘፈነልሽ
ይናገር ልሳንሽ
ይመስክር ገድልሽ
ተአምር ብስራትሽ።

በ1882 ዓ.ም. ጥቅምት ወር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው የነገሱት የኃይለ መለኮት ልጅ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ በአድዋ ጦርነት የኢትዮጵያን ስም በዓለም ያስጠሩ ጀግና መሪ ነበሩ። ምኒልክ ንግሥናቸውን እንዳገኙ የመጀመሪያው የውጭ ጉዳይ ውል ከኢጣልያ ጋር የተደረገው ነበር። ይህም የስምምነት ውል የውጫሌው ውል በመባል ይታወቃል።

የውጫሌ ውል አንቀጽ አሥራ ሰባት የጣሊያንኛው:- *“ኢትዮጵያ ከአውሮጳ መንግሥታት ጋር ማድረግ የምትፈልገውን ግንኙነት በኢጣሊያ መንግስት በኩል ማድረግ አለባት”* ሲል፤
አማርኛው ደግሞ *“ኢትዮጵያ ከአውሮጳ መንግሥታት ጋር ማድረግ የምትፈልገውን ግንኙነት በኢጣሊያ መንግሥት በኩል ማድረግ ትችላለች“*ይላል፡፡

የአማርኛው የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና ልዕልና ሲያስከብር በተቃራኒው የጣሊያንኛው ትርጓሜ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና ልዕልና መድፈር ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ክብሯንና ጥቅሟን ይነካል፡፡

የዳግማዊ ምኒልክ የአርቆ የማሰብ ችሎታ ኢትዮጵያ በኢጣሊያ መንግሥት ቁጥጥር ስር እንዳትገባ ጥረት በማድረግ ነፃነታቸውን ጠብቀው ከሌሎች ሀገራት ጋር ግንኙነትንና ምክር መቀበል ቀጠሉ። በዚህም የተነሳ ኢጣሊያም ኢትዮጵያን ለመያዝ ቁርጥ ሀሳብ አድርጋ በኤርትራ በኩል ትግራይን መውረር ጀመረች። ምኒልክም ሕዝቡን ለጦርነት ክተት አሉ። ታሪካዊው የአፄ ምኒልክ የክተት አዋጅ ነጋሪት እየተጎሰመ ተላለፈ። በጊዜው እንዲህ ተደምጧል:-

***“እግዚአብሔር በቸርነቱ እስካሁን ጠላት አጥፍቶ አገር አስፍቶ አኖረኝ፤ እኔም እስካሁን በእግዚአብሔር ቸርነት ገዛሁ። ከእንግዲህ ብሞትም ሞት የሁሉም ነውና ስለእኔ ሞት አላዝንም። ደግሞ እግዚአብሔር አሳፍሮኝ አያውቅም፤ ወደፊትም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠራጠርም። አሁንም አገር የሚያጠፋ፤ ሃይማኖትን የሚለውጥ፣ በፊት እግዚአብሔር የወሰነልንን ባህር አልፎ መጥቷል። እኔም የአገሬን ከብት ማለቅ፤ የሰውን መድከም አይቼ እስካሁን ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ እንደፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር። አሁን ግን በእግዚአብሔር ረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጠውም። የአገሬ ሰው ከአሁን ቀደም የበደልሁህ አይመስለኝም። አንተም እስካሁን አላስቀየምከኝም። ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ። ጉልበት የሌለህ ለልጅህ፣ ለምሽትህ፣ ለሃይማኖትህ ስትል በሃዘንህ እርዳኝ። ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ። አልምርህም። ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም። ዘመቻዬ በጥቅምት ነውና የሸዋ ሰው እስከ ጥቅምት እኩሌታ ወረይሉ ከተህ ላግኝህ።”***

ጣሊያኖች በጄኔራል ባራቲዬሪ የሚመራውን 20 ሺህ ወታደሮቻቸውን ይዘው በ1888 ዓ.ም. የካቲት 23 ቀን አድዋን ወጉ። ከ 80 ሺህ እስከ 120 ሺህ የሚገመተው የምኒልክ/የኢትዮጵያ ሠራዊትም በሚገባ ሲዋጋ የሀገሪቱ ተፈጥሮአዊ አቀማመጥና ሀገሬን ብሎ በቁርጠኝነት ስሜት ቀፎው እንደተነካ ንብ የተነቃነቀው ኃይል የጠላትን ጦር አደናግጦ መግቢያ መውጫ በማሳጣት ቀኑን ሙሉ ጦርነቱ ከተካሄደ በኋላ በሚያስደንቅ አኳኋን ድሉ የኢትዮጵያ ሆነ። ቅኝ አገዛዝ እግሬ አውጪኝ ሲል ነፃነት ከፍ አለ። በምኒልክ መሪነት ሕዝብ ታሪክ ሰራ። ለጥቁር ሕዝብ የነጻነት ተጋድሎ ጮራው ፈነጠቀ። ኢትዮጵያ በልጆቹዋ ደምና አጥንት ሉዓላዊነቷን አረጋገጠች። በጀግኖቻችን ደም ኢትዮጵያ ክብሯን አገኘች። ልክ የዛሬ 121 ዓመት።

ሃያ ዘጠኝ ሺህ ፈረሰኞችን ጨምሮ ከመቶ ሺህ እስከ መቶ ሃያ ሺህ የሚገመት አንድ ሺህ ኪሎ ሜትር በባዶ እግሩ የተጓዘ የኢትዮጵያ የገበሬ ሠራዊት በወታደራዊ አካዳሚ የሠለጠነውን የአውሮጳ ወራሪ ጦር የካቲት 23 ማለዳ አሥራ አንድ ሰዓት ግድም ገጥሞ ከረፋዱ አራት ሰዓት ላይ ማሸነፉን አረጋግጧል፡፡ የኢትዮጵያ ገበሬ ሠራዊት ፈረሱ ላይ ሆኖ የጋሻውን እምብርት መሬት ላይ እያጠቀሰ ጐራዴውን አየር ውስጥ እየቀዘፈ በወኔ፣ በተቆጣና በቆረጠ መንፈስ በጀግንነት ተዋግቷል፡፡

ጦርነቱ በተጀመረ ከአምስት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሃምሣ ስድስቱም የኢጣሊያ መድፎች ሙሉ ለሙሉ ተማርከዋል፤ የቅኝ ገዢውን ወራሪ ሠራዊት ከመሩት ጄኔራል አልቤርቶኒ ሲማረክ የሠራዊቱ ዋና አዛዥ ጄኔራል ባራቴሪ ከጥቂት አጃቢዎቹና በሽንፈት ከተበታተኑ የኢጣሊያ ወታደሮች ጋር ሸሽቷል፡፡

በዚህ ድብልቅልቅ ያለ ውጊያ ከሃምሣ ስድስቱ የኢጣሊያ መድፎች በተጨማሪ ብዙ ሺህ ቀላልና ከባድ መትረየሶች እንዲሁም የነፍስ ወከፍ ጠመንጃዎች በአሥር ሺሆችና በመቶ ሺዎች ከሚቆጠሩ መሰል ጥይቶቻቸው ጋር ተማርከዋል፡፡ በአጠቃላይ ምርኮው ወደ አዲስ አበባ የተጓጓዘው በአምስት መቶ አጋሰሶች ተጭኖ ነው፡፡

በማግስቱ የካቲት 24 ቀን 1888 ዓ.ም ከጠዋቱ አራት ሰዓት ላይ የኢጣሊያ ምርኮኞች በምኒልክ ድንኳን ፊት ሲያልፉ የኢትዮጵያ ጀግና የገበሬ ሠራዊት እየፎከረ እየሸለለ አሳልፉዋቸዋል፡

የአድዋ ድል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ክብር ማኅተም፤ የጥቁር ህዝቦች የነፃነት ተጋድሎ አክሊል ነው፡፡ አድዋ የታላቅ ህዝቦች ታላቅ ድል ነው፡፡

የአድዋ ድል በአንድ በኩል የቅኝ ገዥዎችን ቅስም የሰበረ ሲሆን በሌላ ገጽታው ቅኝ ተገዥዎችን ለነፃነት ተጋድሎ ያነቃቃ፣ ብርታትና ጥንካሬን ያጎናጸፈ ነው። አድዋ ኢትዮጵያን በዓለም ገናና ያደረገ ነው። ነፃነቷንና ክብሯን ያስጠበቀ ኢትዮጵያዊነትን ከፍ ያደረገ ጦርነት፡ አድዋ ።

የአድዋ ጦርነት በሥልጣን መሻኮትን ወደ ዳር ገፍቶ ሁሉም ለሀገሩና ለሰንደቅ ዓላማው ክተት ያለበት ጦርነት። የሀገር ፍቅርና እምነት የተዋጋበት ጦርነት። የጥቁር ሕዝቦች ድል በአፄ ምኒልክ መሪነት ነጮችን ያሳፈረበት። አፍሪካ የጀግኖች መናኸሪያ መሆኗን ያስመሰከረችበት ጦርነት።

አድዋ ከአዲስ አበባ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ 1066 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም፤ ወይም በአውሮጳውያን የዘመን አቆጣጠር February (የካቲት) መጨረሻ እና March (መጋቢት) መጀመሪያ ላይ 1896.የአድዋ ጦርነት ተካሄደ። ለጦርነቱ መነሻ የሆነው ውል የተፈፀመው በዚሁ ዘመን ከአዲስ አበባ በስተሰሜን 468 ኪሎ ሜትር ርቀት ግድም ከውጫሌ ከተማ ግርጌ ከአምባሰል ተራራ ሥር ወሎ ውስጥ ንጉሥ ይስማ እየተባለ በሚጠራ ሥፍራ ነበር፡፡

በመቶ ሺህ የሚሠላ የኢትዮጵያ ገበሬ ሠራዊት ከአንድ ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የአውሮጳ ቅኝ ገዢ ወራሪዎችን ድባቅ ከመታና ረግጦ ካስወጣ በኋላ የካቲት 23 ቀን ከምሽቱ አራት ሰዓት ግድም እንዳማርያም ላይ ተሰባስቦ በአንድ እግሩ ቆሞ ቀኙን (ድሉን) ለሰጠው አምላክ ምሥጋና አቅርቧል፡፡ *"አባት ሆይ፤ ንቀውን የመጡ የአገራችንን ድንበርና ልዕልና የደፈሩ የአውሮጳ ቅኝ ገዢ ወራሪዎችን እንድናሸንፍ፣ ድል እንድናደርግ ስለረዳኸን እናመሰግንሃለን"*

በአድዋው ጦርነት ሁልጊዜም የሚጠቀሱት የድል እመቤቷ እቴጌ ጣይቱ ዋነኛ ናቸው። እቴጌ ጣይቱ በጡል ለአድዋ ጦርነት መንስኤ የሆነውን የውጫሌ ውል አንቀጽ 17 ኢጣሊያኖች ትርጉሙን አዛብተው ኢትዮጵያን በመዳፋቸው ስር ለማስገባት የሸረቡትን ሴራ ቀድመው ማጋለጣቸው ተነግሮላቸዋል፤ ተጽፎላቸዋል። እቴጌ ጣይቱ ከባለቤታቸው ከአፄ ምኒልክ፣ ከኢትዮጵያውያኑ የጦር አዝማችና ሠራዊታቸው ጋር በመሆን ከተፋፋመው የአድዋው ጦር ግንባር ላይ በመገኘት ጦሩን ከማበረታታት በላይ የመቀሌን ምሽግ በውኃ የሰበሩ ጀግና ናቸው። የመቀሌው የጣሊያን ጦር ምሽግ ጠንካራነት ጣይቱን

ለፈጣን መላ ጋበዘ። ለአጃቢ ወታደሮቻቸው የመስዋዕትነት ግብዣ አቀረቡ ሕይወታችሁን ስጡኝ። የሚገርመው አንደኛ ለመስዋዕትነት የተጋበዙት የተላከንበትን አሸንፈን ተመልሰን መጥተን እንኖራለን የሚል ተስፋ ሰንቀው አይደለም በጀ ያሉት ራሳቸውን ለመስዋዕትነት አዘጋጅተው ነው። ሁለተኛ ጣይቱም ቢሆኑ ጥያቄያቸው ትሰዋላችሁ ነው። የሚገርመው የጣይቱ የመስዋዕትነት ክፍያው ነው። ማጭበርበር የለ፣ ታሪክ ያስታውሳችሁዋል የለ፣ ሀውልት ይቆምላችሁዋል የለ፣ ስማችሁ ይጠራል የለ። ለቆማችሁት እሸልማለሁ፣ ለምታልፉ ተዝካራችሁን አወጣለሁ፣ የሙት ልጆቻችሁን አሳድጋለሁ! በቃ። ከ600- 900 ወታደሮች ቀርበው ተሰናብተው ሄዱ። ከዛ ያለፈው ታሪክ ነው። እነዚያ ወታደሮች የመቀሌውን የጣሊያን ጦር የመጠጥ ምንጭ ያዙ። ጣሊያን የሆዱ ነገር አሸነፈውና የመቀሌው ምሽጉ ባስደናቂ ሁኔታ ተሰበረ። የጣይቱ ብልህነት ወራሪውን ጣልያን ድል መታ።

"አንድ ሀገር አንድ ሕዝብ ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" የአድዋን 121ኛ ዓመት ክብረ በዓል ስንዘክር የታሪኩን አስተማሪነትና ኢትዮጵያውያን ለሀገራችን ያለንን ፍቅርና ክብር እየኮራንበት ነው። አድዋ በምኒልክ የከተተ አዋጅ ውስጥ መተባበርን፣ እምነትን፣ መስዋዕትነትን፣ ፍቅርን ያስተምረናል። አድዋ በሰው ልጆች ዘንድ ብቀላና ቂም በቀል እንዳይኖር በጣልያን ምርከኞችና በአስተዋይ መሪው ምኒልክ ይቅር ባይ ውሳኔ ያመላክተናል። አድዋ ለሀገር አንድነትና ነፃነት የሚፈስ ደም ክቡር መሆኑን በጀግኖቻችን ውስጥ ያሳየናል። አድዋ ወረራ፣ ጦርነት፣ ትዕቢት መጨረሻው ውርደት መሆኑን ይተርክልናል። አድዋ የሰው ልጅ በሰውነቱ እኩል መሆኑን፣ ክብሩን ፈላጊ፣ መብቱን አስከባሪ ለመሆኑ ምስክር ነው።

ዛሬ ሀገራችን ማንነቷና ክብሯ በህወሀት/ኢሕአዴግ ቢገፈፍም አድዋ ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ መድረክ እንድትታወቅና እንድትከበር ምክንያት ሆኗል። ዛሬ ገንዘብ ለሰጠው ሁሉ በሚሰግደው ወያኔ/ህወሀት አምላኪ ነጭ ሀገራችንን ለባዕዳን አሳልፎ ቢሰጥብንም አድዋ የኢትዮጵያዊነትን ብቻ ሳይሆን የጥቁር ሕዝቦችን ክብር ከፍ አድርጎ ዘረኝነትን የቀበረ ታሪካችን ነው። መብትና ነፃነት በተጋድሎና በመስዋዕትነት የሚቀዳጁት መሆኑን አድዋ ያስታውሰናልና ሀገርን ከወያኔ/ኢሕአዴግ መድፍ ፈልቅቆ የልጆቿ ለማድረግ በኢትዮጵያዊነት ጥላ ስር ክተት ለማለት መዘጋጀት ይኖርብናል። ዛሬ ሀገር የሚያጠፋ፣ ሃይማኖት የሚበርዝ፣ ድንበርን የሚቆርስ፣ ሕዝብን የሚያባላ፣ ታሪክ የሚያጠፋ ሀገር በቀል ወራሪ ወያኔ ነውና በጋራ ታግለንና ጥለነው ሀገርና ሕዝብ ከተደቀነባቸው አስከፊ አደጋ ልንታደግ የምንችለው በጋራና በሕብረት ሁሉም ሲጠራራ ነውና እምቢልታው ይነፋ፣ ነጋሪት ይመታ እንላለን።

ክብር ለአድዋ ሰማዕታት!!!

**ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!**
**እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!**
**"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"**

የካቲት 23 ቀን 2009 ዓ.ም. (March 01, 2017)

**ዋቢ ማጣቀሻ :-**

- ውክፔድያ ነፃው መዝገበ ዕውቀት
- ጆርጅ በርክሊይ "የአድዋ ጦርነትና ዳግማዊ አፄ ምኒልክ"፤ ትርጉም ዳኛቸው ኃይሌ
- አእምሮ ልዩ ዕትም የካቲት 2008 ዓ.ም.

**ማሳሰቢያ ፡**

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» «*ኢትዮጵያችን*» ልሳን በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com
ምስለ ገጽ : Ethiopiachen Hagerachen

You Tube :- https://www.youtube.com/watch?v=gWFHRGeJ2kM